የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

# ሶማሊ፦ በኢሰመኮ የተሰጡ ምክረ ሐሳቦችን ለመፈጸም ክልሉ የወሰዳቸውን ተጨባጭ እርምጃዎች በተመለከተ

*የሶማሊ ክልል በአጭር ጊዜ ውስጥ የወሰዳቸው እርምጃዎች በሌሎች ክልሎች በአርዓያነት ሊወሰዱ የሚገባቸው ናቸው*

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ጋዜጣዊ መግለጫ
ኅዳር 16 ቀን 2018 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በሶማሊ ክልል ያለውን አጠቃላይ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በተመለከተ ከክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጋር ጥቅምት 10 ቀን 2018 ዓ.ም. በጅግጅጋ ከተማ ውይይት ማካሄዱ ይታወሳል። በውይይቱ ኢሰመኮ በክልሉ ያለውን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በተመለከተ በተለያየ ጊዜ ባካሄዳቸው ክትትሎች የደረሰባቸውን ግኝቶች በማቅረብ መልካም እመርታዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ እና አሳሳቢ ጉዳዮች የእርምት እርምጃ እንዲወሰድባቸው አሳስቧል። በተለይም በማረሚያ ቤቶች እና በፖሊስ ጣቢያዎች በሕግ ጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎች የሰብአዊ መብቶች አያያዝ እና የፍትሕ ተደራሽነት እንዲሻሻል ለማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎች እንዲወሰዱ እንዲሁም የተራዘመ የቅድመ ክስ እስራት ሁኔታ እንዲታረም ለተፋጠነና የተሟላ ፍትሕ አሰጣጥ በቂ ትኩረት እንዲሰጥ ኢሰመኮ ምክረ ሐሳብ አቅርቧል።

የሶማሊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ክቡር ሙስጠፋ መሀመድ በውይይቱ ላይ ኢሰመኮ በዝርዝር ያነሳቸው አሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮችን እልባት ለመስጠት በተለይም የተራዘመ የቅድመ ክስ እስራትን በማስቀረት የተፋጠነ ፍትሕ ሥርዓትን ለመተግበር የክልሉ መንግሥት በልዩ ትኩረት እንደሚሠራ እና ክትትል እንደሚያደርግ በገቡት ቃል መሠረት ክልሉ አበረታች ተግባራዊ እርምጃዎችን መውሰድ መጀመሩን ኢሰመኮ ለማረጋገጥ ችሏል። በዚሁ መሠረት በክልሉ በተለያዩ ፖሊስ ጣቢያዎች ከሕግ አግባብ ውጪ ታስረው የነበሩ በአጠቃላይ 121 ሰዎች ከእስር መለቀቃቸውን እንዲሁም ሌሎች ትኩረት የሚፈልጉ አሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮችን ለማስተካከል ክልሉ ጥረቶችን በማድረግ ላይ መሆኑን ለመገንዘብ ችሏል። በተጨማሪም ክልሉ ተፈርዶባቸው በማረሚያ ቤቶች የነበሩ 2 ጋዜጠኞችን በይቅርታ መልቀቁን ኢሰመኮ አረጋግጧል።

የኢሰመኮ ዋና ኮሚሽነር ብርሃኑ አዴሎ የሶማሊ ክልል በአጭር ጊዜ ውስጥ ለወሰዳቸው አበረታች የምክረ ሐሳቦች አፈጻጸም እርምጃዎች ዕውቅና ሰጥተው፣ ተግባሩ በሌሎች ክልሎችም በአርዓያነት ሊወሰድ የሚገባው መሆኑን ገልጸዋል። ክልሉ ሌሎች አሳሳቢ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮችን መፍትሔ ለመስጠት የጀመራቸውን ጥረቶች እንዲያጠናክር አሳስበው፣ ኢሰመኮ በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን ለማሻሻል በክልሎች ደረጃ የሚያደርጋቸውን የውትወታና የምክረ ሐሳቦች አፈጻጸም ክትትል ሥራዎች አጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል።

. . . .

**ለተጨማሪ መረጃ:-**

**በዳሳ ለሜሳ** (አማርኛ፣ አፋን ኦሮሞ፣ እንግሊዘኛ)
ከፍተኛ ዳይሬክተር
የሰብአዊ መብቶች ክትትልና ምርመራ ሥራ ክፍል



ይጎብኙን፣ መረጃዎቻችንን ይከተሉ
Facebook | Twitter | YouTube | LinkedIn: @EthioHRC - https://ehrc.org/
በነጻ የስልክ መሥመራችን 7307 ላይ በመደወል የሰብአዊ መብቶች ጥሰት አቤቱታ ማቅረብ ወይም ጥቆማ መስጠት ይችላሉ

ኢሰመኮ
badassa.lemessa@ehrc.org
+251 911 86 04 60

አሸር አህመድ (አማርኛ፣ ሶማሊኛ፣ እንግሊዘኛ)
ኃላፊ
ጅግጅጋ ጽሕፈት ቤት
ኢሰመኮ
asher.ahmed@ehrc.org
+251912892760

## ስለ ኢሰመኮ

**የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በፌዴራል ሕገ መንግሥቱ መሠረት ነጻ ፌዴራላዊ መንግሥት አካል ሆኖ የተቋቋመና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆነ ለሰብአዊ መብቶች መስፋፋት፣ መከበር እና ጥበቃ የሚሠራ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ነው። (የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/14 እና አዋጅ ቁጥር 210/1992 በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው)**